# የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት

## በውጪ ፈንድ (መዋዕለ-ንዋይ) የሚደገፉ ፕሮጀክቶች ትግበራ ለሚሳተፉ አመራሮች እና ባለሙያዎች የማትጊያ ክፍያ አፈፃጸም መመሪያ

ጥቅምት 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ



መለሰ ማርዮ ሰላሞ (ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት ለሀገራችን የተፋጠነ እድገት መሰረት የሆነውን ዘርፈ ብዙ የብዝሀ ሕይወት ሀብት ጥበቃን በምርምር በተደገፈ አሰራር በተገቢው መንገድና በተፈለገው ልክ ታውቆ እንዲነበር፤ አሁን ያለው የብዝሀ ሕይወት ሃብት እንዳይመናመን የሚያስችል ዘለቄታዊ አጠቃቀም እንዲተገበር እና ከብዝሀ ሕይወት የሚገኝ ጥቅም ሚዛናዊና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የማህበረሰብ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ እየሰራ ያለ የምርምር ተቋም በመሆኑ፣

እነዚህ መጠነ ሰፊ ስራዎች በመንግስት በጀት የሚከናወኑ ሲሆን፤ የተወሰኑት ደግሞ በብዝሀ ሕይወት ላይ በሚሰሩና ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው የውጪ ተቋማት በሚገኝ ፈንድ የሚደገፉ ፕሮጀክቶች ይተገበራሉ፡፡

ስለሆነም የኢንስቲትዩቱ ተመራማሪዎች የተቋሙን ብሎም የሀገርን አቅም ለመገንባት በልዩ ትኩረት አዳዲስ ፕሮጀክቶች ንድፈ ሀሳቦችን እንዲያዘጋጁና የውጪ ፈንድ እንዲያፈላልጉ ለማትጋት፤

እነዚህ ፕሮጀክቶች በጊዜ ገደብ የሚተገበሩ እንደ መሆናቸው መጠን አደረጃጀታቸውም በተወሰነ መልኩ ከመደበኛው ወይም በመንግስት ከሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ለየት ያለና ልዩ ትኩረት የሚሹ በመሆናቸው፣

ፕሮጀክቶች ትኩረት ባደረጉባቸው ተግባራት መሰረት እስከ ማህበረሰብ ደርሰው የሚፈጸሙ በመሆናቸው አሰራራቸው ግልጽነትና ወጥነት ያለው እንዲሆንና ያለ መጓተት እንዲፈጸሙ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የፕሮጀክቶቹን ዓላማ ለማሳካት እንዲሁም ውጤታማ ለማድረግ ይረዳ ዘንድ ሌሎች የምርምር ተቋማትን ምርጥ ተሞክሮ በመዳሰስ ይህ በውጪ ፈንድ (መዋዕለ-ንዋይ) የሚደገፉ ፕሮጀክቶች ትግበራ ለሚሳተፉ አመራሮች እና ባለሙያዎች የማትጊያ ክፍያ አፈፃፀም መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡



መለሰ ማርዮ ሰላም(ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 1
### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት በውጭ ፈንድ የሚደገፉ የምርምርና አቅም ግንባታ ኘሮጀክቶችን በማምጣት፣ በመምራት (በማስተባበር) እና በመተግበር ከመደበኛ ሥራ ጎን ለጎን ለሚሳተፉ ባለሙያዎች እና አመራሮች የማትጊያ ክፍያ የውስጥ መመሪያ ቁጥር ------/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### አንቀጽ 2
### ትርጓሜ

1. **"ኢንስቲትዩት"** ማለት የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት ሲሆን፣ ዋና መስሪያ ቤትንና በስሩ የሚገኙ የብዝሀ ሕይወት ማዕከላትን፣ የዕፅዋት አፀዶችን፣ ዱፕሊኬት ጅን ባንክን፣ የመስክና ማህበረሰብ ጅን ባንኮችን ያጠቃልላል።
2. **"በውጪ ፈንድ የሚደገፉ ፕሮጀክቶች"** ወይም **"ፕሮጀክት"** ማለት ከውጪ አገር በሚገኝ የገንዘብና የዓይነት ድጋፍ የሚተገበሩ ማናቸውም ፕሮጀክቶች ማለት ነው።
3. **"የፕሮጀክት አስተባባሪ"** (Project Coordinator) ማለት በውጭ ፈንድ የሚደገፍ ፕሮጀክት እንዲያስተባብር በኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር የተመደበ አስተባባሪ ወይም ፕሮጀክት እንዲያስተባብር የተቀጠረ ባለሙያ ወይም በውጪ ፈንድ የሚደገፉ ፕሮጀክቶችን ተጻጽፎ ያመጣ ባለሙያ ነው።
4. **"የኘሮጀክት ዋና ተመራማሪ"** (Project Principal Investigator) ማለት በውጭ ገንዘብ የሚደገፍ የምርምር እና አቅም ግንባታ ኘሮጀክትን ተፃፅፎ ያስገኘ ወይንም በተቋሙ የተገኘ ኘሮጀክትን በዋና ተመራማሪነት እንዲተገብር የምርምር ብቃትን መሠረት ባደረገ ግልፅ መስፈርቶች በሚመለከታቸው የሙያ ዘርፉ ወይም የተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች የተመደበ ተመራማሪ ማለት ነው፤
5. **"የኘሮጀክት ተባባሪ ተመራማሪ"** (Project Co-Principal Investigator) ማለት በሚመለከታቸው የተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች ወይንም ፕሮጀክት አስተባባሪዎች ዋና



መሰስ ማርዮ ሰላም(ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

ተመራማሪውን በፕሮጀክት ትግበራ እንዲያግዝ የፕሮጀክቱን ዓላማ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅምን መሠረት ባደረገ ግልፅ መስፈርቶች በረዳትነት የሚመደብ ተመራማሪ ነው፤

6. **"የፕሮጀክት ትግበራ ተጠሪ"** (Project Focal Person) ማለት በውጭ ፈንድ የሚደገፉ ፕሮጀክቶችን አጠቃላይ ሂደት እንዲያቀናጅ፣ እንዲከታተል፣ ሪፖርት እንዲዘጋጅና እንዲያቀርብ በኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር የሚመደብ የኢንስቲትዩቱ ባለሙያ ነው፡፡
7. **"የፕሮጀክት ማኔጅመንት ቡድን"** ማለት በውጭ ፕሮጀክቶች ትግበራ ሂደት ውስጥ ተከታታይና ቀጥተኛ ተሳታፊ የሆኑ አመራሮች፣ ባለሙያዎች እና የፋይናንስና ሌሎች የአስተዳደር ዘርፍ ሠራተኞችን ያካትታል፡፡

### አንቀጽ 3
### ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ በኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት በውጪ ፈንድ የሚደገፉ ፕሮጀክቶች ውጤታማ እንዲሆኑና በአግባቡ እንዲፈጸሙ ለማስቻልና ባለሙያዎች አዳዲስ ፕሮጀክቶችን እንዲቀርፁና ፈንድ እንዲያፈላልጉ ለማትጋት ነው፡፡

### አንቀጽ 4
### የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በኢንስቲትዩቱ የሚተዳደሩ በኢንስቲትዩቱ ውስጥ በቀጥታ ወይም ከሌሎች ተቋማት ጋር በትብብር የሚተገበሩ በውጪ ፈንድ የሚደገፉ ፕሮጀክቶች ላይ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## በውጪ ፈንድ የሚደገፉ ፕሮጀክቶች አፈፃጸም

### አንቀጽ 5
### በውጪ ፈንድ የሚደገፉ ፕሮጀክቶች ላይ ተግባራዊ የሚደረጉ ህጎች

በውጪ ፈንድ የሚደገፉ ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም በተመለከተ በዋናነት በተለያዩ የፕሮጀክት ሰነዶች የተመለከቱ አሰራሮችና አፈጻጸሞች እንደተጠበቁ ሆነው አግባብነት ያላቸው የመንግስት አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተፈጻሚ ይደረጋሉ፡፡



መለሰ ማርዮ ሰላሞ(ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

## አንቀጽ 6

## የፕሮጀክት ተጠሪነት

በውጪ ፈንድ የሚደገፍ ፕሮጀክት ተጠሪነቱ ለኢንስቲትዩቱ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 7

## የፕሮጀክት አስተባባሪ ስለመሰየም

1. የፕሮጀክት አስተባባሪ የሚሰየመው በፕሮጀክት ሰነዱ በተገለጸው መሠረት ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን የፕሮጀክት አስተባባሪ አሰያየምን በተመለከተ በፕሮጀክት ሰነዱ ውስጥ የተገለጸ ነገር ከሌለ፤ በውድድር ወይም በኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር የሚሰየም ይሆናል፡፡
2. የፕሮጀክት አስተባባሪው የተሰየመው ከኢንስቲትዩቱ ከሆነና የሙሉ ጊዜ የፕሮጀክት አስተባባሪ ከሆነ የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 47 (3) ተግባራዊ ይደረጋል፡፡
3. ተመራማሪዎች በውጭ የሚደገፍ ፕሮጀክቶችን ተፃፅፈው እንዲያመጡ፣ ፕሮጀክቶችም ሲገኙ በጥራት እና ስምምነት በተደረሰበት የጊዜ ገደብ መከናወን ስለሚገባቸው ክህሎት፣ የዳበረ ልምድና በቂ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው ተመራማሪዎች የሚኖራቸውን ተሳትፎ ማጉላት የተቋሙን ውጤታማነት ከማሳደግ አንፃር ወሳኝ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ተመራማሪዎች በፕሮጀክቶች የማስተባበርና በዋና ተመራማሪነት የሚኖራቸውን የተሳትፎ መጠን የትምህርት ዝግጅትን፣ የምርምር እና የማኔጅመንት ልምድን በማገናዘብ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡
    3.1. በረዳት ተመራማሪ II እና ተባባሪ ተመራማሪ የሥራ ደረጃ የሚገኙ በአንድ ወቅት (ተመሣሣይ ወቅት) በአንድ ፕሮጀክት የማስተባበር ወይም ግንባር ቀደም ተመራማሪነት ብቻ ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ግን በዚህ ፈርጅ የሚገኙ ተመራማሪዎችን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም በማገናዘብ የተቋሙ የበላይ ሃላፊ ተጨማሪ አንድ ፕሮጀክት እንዲያስተባብሩ ሊወስን ይችላል፡፡
    3.2. በተመራማሪ I እና II የሥራ ደረጃ የሚገኙ በአንድ ጊዜ (ተመሳሳይ ወቅት) ፕሮጀክቶች የሚጠይቁት የሥራ ጊዜ እየታየ እስከ ሁለት በሚደርሱ ፕሮጀክቶች በአስተባባሪነት ወይንም በዋና ተመራማሪነት ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡
    3.3. በከፍተኛ እና መሪ ተመራማሪ የሥራ ደረጃ የሚገኙ ተመራማሪዎች በአንድ ወቅት (ተመሳሳይ ጊዜ) እስከ ሦስት በሚደርሱ ፕሮጀክቶች በአስተባባሪነትና በዋና



መለሰ ማርዮ ሰላሞ (ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

ተመራማሪነት ሊሳተፉ ይችላሉ። ሆኖም ግን ኘሮጀክቶቹ የሚፈልጉት የሥራ ጊዜና ተመራማሪው ያለበት የስራ ኃላፊነትና ጫና እየተመዘነ እና እየተገመገመ በተቋሙ የበላይ ማኔጅመንት የሚወሰን ይሆናል።

4. የፕሮጀክት አስተባባሪው በስራው የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ላይ በማይገኝበት ወቅት ተጠሪ ከሆነበት ኃላፊ ጋር በመመካከር ብቁ አስተባባሪ ይወከላል።
5. የፕሮጀክት አስተባባሪው በስራው የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ላይ ከሶስት ወርና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ አለመገኘቱ ሪፖርት ሲቀርብ የፕሮጀክት ስራውን በጊዜያዊነት የሚያስተባብር ብቁ አስተባባሪ በዋና ዳይሬክተር ይወከላል።

## አንቀጽ 8

## የፕሮጀክት አስተባባሪ ተጠሪነት

የፕሮጀክት አስተባባሪ ተጠሪነቱ ለኢንስቲትዩቱ ይሆናል።

## አንቀጽ 9

## የፕሮጀክት አስተባባሪና ፕሮጀክቱን የሚመሩ ኃላፊዎች የሥራ ድርሻ

የፕሮጀክት አስተባባሪው በፕሮጀክት ሰነዱ በዝርዝር የተመለከተውን የፕሮጀክት አስተባባሪ ተግባርና ኃላፊነት በብቃት እንዲወጣ ድጋፍ ይደረግለታል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች የሚመለከታቸው ማለትም ዋና ዳይሬክተሩ፣ ም/ዋና ዳይሬክተሩ ወይም (መሪ) ሥራ አስፈፃሚዎች የፕሮጀክት አስተባባሪው የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በብቃት እንዲወጣ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋሉ።

## አንቀጽ 10

## የፕሮጀክት ስራን በትብብር ስለመፈጸም

1. የፕሮጀክት አስተባባሪው በፕሮጀክት ሰነዱ ላይ በተቀመጠው መሰረት ፕሮጀክቱን ይመራል/ያስተባብራል።
2. የኢንስቲትዩቱ የስልጠና ማማከር፣ ፕሮጀክት ድጋፍና ክትትል መሪ ስራ አስፈጻሚ በፕሮጀክት ሰነዱ የተቀመጡ የፕሮጀክት ስራዎች ከመደበኛ ስራዎች ጋር ተቀናጅተው በጥራት፣ በመጠንና በጊዜ እንዲተገበሩ የማሳለጥ፤ እንዲሁም የፕሮጀክት አፈጻጸምን አስመልክቶ የድጋፍ፣ ክትትልና ግምገማ ስራን ይመራል/ያስተባብራል።



መለሰ ማርዎ ሰላም(ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

## አንቀጽ 11

## የፕሮጀክት ፋይናንስ ዘርፍ ስለማደራጀት

1. በፕሮጀክት ጽንስ-ሃሳብ ቀመራ፣ ሰነድ ዝግጅት እና የውል ስምምነት ወቅት የፕሮጀክት ፋይናንስ ዘርፍ የሰው ኃይል እንዲሟላ ይደርጋል።
2. የኢንስቲትዩቱ የፕሮጀክት ፋይናንስ ዘርፍ ተጠሪነቱ ለግዢና ፋይናንስ ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ የቡድን መሪ፣ የበጀት ተቆጣጣሪ እና የፕሮጀክቱ ፋይናንስ ሠራተኛ ይኖራቸዋል።
3. የፕሮጀክት ፋይናንስ ሠራተኞች የፕሮጀክቱ ቀጥታ ተቀጣሪዎች እንደመሆናቸው ደመዛቸው በቀጠራቸው ፕሮጀክት የሚሸፈን ሲሆን፣ የፕሮጀክት ፋይናንስ ዘርፍ የቡድን መሪ እና የበጀት ተቆጣጣሪ ከፕሮጀክቶች በሚዋጣ በጀት ደመወዛቸው የሚሸፈን ይሆናል።
4. የፕሮጀክት ፋይናንስ ዘርፍ የፕሮጀክቱን ፋይናንስ ሂደት ኦዲት ያስደርጋል፣ ለተገቢው የኦዲትና ቁጥጥር ሥራ ትብብርና ድጋፍ ያደርጋል፣ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል።

## አንቀጽ 12

## የፕሮጀክት የሰው ኃይል ቅጥር

የፕሮጀክት የሰው ኃይል ቅጥር በፕሮጀክት ሰነዱ በተመለከተው መሰረት በፕሮጀክት አስተባባሪው ተጠይቆ በዋና ዳይሬክተር ሲፀድቅ በኢንስቲትዩቱ የብቃትና ሰው ሃብት ልማት አስተዳደር ስራ አስፈጻሚ አማካይነት ይፈጸማል።

## አንቀጽ 13

## የፕሮጀክት ንብረት አጠቃቀም

የፕሮጀክቱ ንብረት በዋናነት የፕሮጀክት ተግባራትና ዓላማ ማስፈጸሚያ የሚውሉ ሆኖ አጠቃቀምና አስተዳደራቸው በመንግስት ህግ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት ይሆናል።

## አንቀጽ 14

## የፕሮጀክት አፈጻጸም ዕቅድና ሪፖርት

1. በፕሮጀክቱ ዓመታዊ ዕቅድ ላይ የተመሰረተ ወቅታዊ የፕሮጀክት እቅድና የአፈፃፀም ሪፖርት ለስልጠና ማማከር፣ ፕሮጀክት ድጋፍና ክትትል መሪ ስራ አስፈጻሚ ይቀርባል፣ የአፈፃጸም ግምገማ ይደረጋል፣ ግብረ መልስም ይሰጣል።

መለሰ ማርቆ ለላሞ(ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

2. በየሩብ ዓመት የተከፋፈለ የፕሮጀክቱ የፊዚካል ስራና የበጀት ዓመታዊ እቅድ በስልጠና ማማከር፣ ፕሮጀክት ድጋፍና ክትትል መሪ ስራ አስፈጻሚ በኩል በም/ዋና ዳይሬክተሩ ወይም በዋና ዳይሬክተሩ ተገምግሞ ለስትራቴጂክ ጉዳዮች ስራ አስፈጻሚ፣ ለፈንድ ድጋፍ ሰጪ አካላትና ለገንዘብ ሚኒስቴር ይቀርባል፡፡

3. የፕሮጀክቱ የፊዚካል ስራና የፋይናንስ አፈፃፀም በየሩብ ዓመቱ በፕሮጀክት አስተባባሪው አማካይነት ተዘጋጅቶና በኢንስቲትዩቱ የስልጠና ማማከር፣ ፕሮጀክት ድጋፍና ክትትል መሪ ስራ አስፈጻሚ ተጠናቅሮ በም/ዋና ዳሬክተር ወይም በዋና ዳይሬክተር ታይቶ ለኢንስቲትዩቱ ስትራቴጂክ ጉዳዮች በኩል ለሚመለከታቸው ሌሎች መሪ/ ስራ አስፈጻሚዎች፣ ለገንዘብ ሚኒስቴር እና ለሚመለከተው ድጋፍ ሰጪ አካል ሪፖርት ይቀርባል፡፡

## ክፍል ሦስት

### በውጭ ፈንድ በሚደገፉ ፕሮጀክቶች የሚፈጸሙ ልዩ ልዩ ክፍያዎችና ጥቅማጥቅሞች በተመለከተ፤

### አንቀጽ 15

### በፕሮጀክት ትግበራ ላይ ለሚሳተፉ አመራሮችና ባለሙያዎች የሚፈፀም ክፍያ፤

1. ለማትጊያ ክፍያ የሚያዝ በጀትን በተመለከተ፤
ለፕሮጀክት ማስተባበሪያ እና ትግበራ ማትጊያ (Staff time, Personnel or Honorarium) የሚያዘው በጀት ከጠቅላላው በጀት 25 በመቶ መብለጥ የለበትም፡፡ ሆኖም የፕሮጀክቱ ፀባይ አስገዳጅ ሆኖ ሲገኝ የበላይ ኃላፊዎችን በማማከር በልዩ ሁኔታ ሊታይ ይችላል፡፡

2. በውጭ ገንዘብ ድጋፍ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ለማሳለጥና ተጠባቂ ውጤቶች በጥራትና በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ እንዲቀርቡ ለማድረግ እንዲቻል በፕሮጀክት ለሚሳተፉ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የገቢ ግብር የሚከፈልበት ተመጣጣኝ ማትጊያ እንደሚከተለው ይከፈላል፡፡ የማትጊያ ክፍያው የሚፈፀመው ፕሮጀክቶቹ በቂ በጀት ካላቸውና በስምምነት ሰነዱ በግልፅ ማትጊያ (Staff time, Personnel or Honorarium) በሚል ሲሰፍር ይሆናል፡፡ በውጭ ገንዘብ ድጋፍ የሚተገበር ፕሮጀክትን ለሚመራ አስተባባሪ (Project Coordinator)፣ ዋና ተመራማሪ (Principal Investigator) ፣ ተባባሪ ተመራማሪ (Co-Principal Investigator)፣ እና የፕሮጀክት ተጠሪ (focal persons) በፕሮጀክቱ የውል ስምምነት ሰነድ በተቀመጠው

መለሰ ማሮ ሰጣሞ(ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

መሠረት የማትጊያ ክፍያ ይከፈላል። አንድ ኘሮጀክት አንድ አስተባባሪ የሚኖረው ሲሆን፣ እንደ ኘሮጀክቱ ይዘት እና ተጠባቂ ውጤቶች ከአንድ በላይ ዋና ተመራማሪ፣ ተባባሪ ተመራማሪ እና የኘሮጀክት ተጠሪ ሊኖር ይችላል። ሆኖም ግን እንደ ኘሮጀክቱ ሁኔታ የኘሮጀክት አስተባባሪው የዋና ተመራማሪነትን የሥራ ድርሻ ደርቦ ሊይዝ ይችላል።

3. ለኘሮጀክት ማስፈፀሚያ በቂ የማትጊያ በጀት (Staff time, Personnel or Honorarium) ተመድቦ፤ ሆኖም አፈፃፀሙን በተመለከተ በኘሮጀክቱ የውል ስምምነት ሰነድ በጥቅል የተቀመጠ ከሆነ ወይንም ኘሮጀክቱን በገንዘብ የሚደግፈው አጋር ድርጅት በኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት የውስጥ መመሪያ እንዲከናወን ካመለከተ ወይንም ዝርዝሩ በማያሻማ ሁኔታ ያልተገለፀ ከሆነ ወይንም የፕሮጀክት ማኔጅመንቱ ተገቢ ሆኖ በሚያገኘው ማንኛውም ምክንያት የማትጊያ ክፍያው እንደሚከተለው ይፈፀማል።

3.1 ለኘሮጀክት አስተባባሪ (Project Coordinator) /ዋና ተመራማሪ (Principal Investigator) ለእያንዳንዳቸው በወር 20,000 (ሃያ ሺህ) ብር ይከፈላል፤ሁለቱንም ስራ አንድ ሰው ደርቦ የሚሰራ ከሆነ ክፍያውን በአንዱ ብቻ የሚከናወን ይሆናል።

3.2 ለተባባሪ ተመራማሪ (Co-principal Investigator) 15,000 (አስራ አምስት ሺህ) ብር ይከፈላል፤

3.3 ለኘሮጀክት ተጠሪ (Focal Person) በወር 6,000 (ስድስት ሺህ) ብር ይከፈላል፤

3.4 ከላይ ከ3.1 — 3.3 መሠረት የተመለከተውን መጠን ለመክፈል ለማትጊያ የተመደው በጀት በቂ ሳይሆን ሲቀር የኘሮጀክቱ አስተባባሪ ከተቋሙ የበላይ ኃላፊ ጋር በመመካከር የክፍያው መጠን ይወሰናል፤

4. የውጭ ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ከማሳለጥ አንፃር የተቋሙ የበላይ ማኔጅመንት፣ የስልጠና ማማከርና፣ ፕሮጀክት ድጋፍና ክትትል መሪ ስራ አስፈጻሚ እና የአስተዳደር ዘርፍ ስራ አስፈጻሚዎች ከመደበኛው ስራቸው በተጨማሪ ለፕሮጀክቶች ትግበራ ውጤታማነት ጉልህ ሚና እንዳላቸው ይታመናል። እነዚህ የተቋሙ ባልደረቦች ከሥራቸው ፀባይ አኳያ ከአንድ ወይንም ከተወሰነ ኘሮጀክቶች ብቻ ጋር አስተዋፆአቸውን ማያያዝ ያስቸግራል። በመሆኑም እነዚህ የተቋሙ ባልደረቦች ኘሮጀክቶች ለአጠቃላይ አስተዳደራዊ እና የጋራ መገልገያ ወጪዎች (Overhead Cost) ከሚሰባሰብ ቋት እንደሚከተለው ይከፈላል።

4.1 የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር እና ምክትል ዋና ዳይሬክተር እያንዳንዳቸው በወር 10,000 (አስር ሺህ) ብር፤

መለሰ ማርዮ ሰባሞ(ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

4.2 የስልጠና ማማከርና፣ ፕሮጀክት ድጋፍና ክትትል መሪ ስራ አስፈጻሚ በወር 10,000 (አስር ሺ.ህ) ብር፤

4.3 የስራ አመራር ዋና ሥራ አስፈፃሚ በወር 5,000 (አምስት ሺ.ህ) ብር፤

4.3 የስትራቴጂክ ጉዳዮች ስራ አስፈጻሚ በወር 5,000 (አምስት ሺ.ህ) ብር፤

4.4 የፋይናንስ ዳይሬክተር እና የውጭ ኘሮጀክቶች የፋይናንስ ክፍል ኃላፊ እያንዳንዳቸው በወር 5,000 (አምስት ሺ.ህ) ብር፤

4.5 የምርምር ማዕከላት በውጭ የገንዘብ ድጋፍ የሚከናወኑ ኘሮጀክቶች የሚተገበሩባቸው በመሆኑ የዕለት ተዕለት አስተዳደራዊ ድጋፍ ለሚያደርጉ የማዕከሉ ማኔጅመንት ማትጊያ መክፈል ተገቢ ይሆናል። በመሆኑም ማዕከላት በውጭ ገንዘብ ድጋፍ ከሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ለአጠቃላይ አስተዳደራዊ እና የጋራ መገልገያ ወጪዎች (Overhead Cost) የሚያሰባስቡት አመታዊ ገንዘብ 200,000 (ሁለት መቶ ሽህ) ብር እና በላይ ሲሆን ለማዕከል ዳይሬክተር 4,500 (አራት ሽህ አምስት መቶ)፣ የፋይናንስ የስራ ሂደት ተጠሪ እና የኘሮጀክት አካውንታንት እያንዳንዳቸው 2,000 (ሁለት ሽህ) ብር የማትጊያ ክፍያ ይከፈላል።

### አንቀጽ 16

### ፕሮፖዛል አዘጋጅተው ፈንድ ለሚያመጡ ግለሰቦችና ቡድኖች የሚከፈል የማትጊያ ክፍያ፤

1. ከውጭና ከተለያዩ ምንጮች ፈንድ በማፈላለግ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል በማዘጋጀት ፈንድ ለሚያመጡ ግለሰቦች/ቡድን ክፍያ እንደሚከተለው ይሆናል፤
   1.1. ከ50 ሺ.ህ እስከ 100 ሺ.ህ ዶላር 5%፣
   1.2. ከ101 ሺ.ህ እስከ 500 ሺ.ህ ዶላር 4%፣
   1.3. ከ501 ሺ.ህ እስከ 1 ሚሊዮን ዶላር 3%፣
   1.4. ከ1 ሚሊዮን ዶላር በላይ 2% ይከፈላቸዋል። ይህም የሚተገበረው ከላይ ከተገለጸው ማትጊያ በተጨማሪ ነው።
2. በቡድን ተዘጋጅቶ የውጭ ፈንድ ለተገኘበት ፕሮጀክት አከፋፈል የቡድኑ አባላት እንደየተሳትፏቸው ተስማምተው በሚያቀርበው የስሌት መጠን መሰረት ይሆናል። ነገር ግን በስሌቱ ስምምነት ላይ ካልደረሱ የተቋሙ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ይሰጣል።



መለሰ ማርዮ ሰላሞ(ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

## አንቀጽ 17

## በውጪ ፈንድ የሚደገፍ ፕሮጀክት በሚመለከት የተለያዩ ዶክመንቶችን ለሚያዘጋጁ፣ የጥናት ጽሁፎችን በአውደ ጥናት፣ ሴሚናር፣ ስልጠና እና ሌሎች ተመሳሳይ ሥራዎች ላይ ለሚያቀርቡ ግለሰቦችና ቡድኖች የሚከፈል የማትጊያ ክፍያ

ተመራማሪዎችና የምርምሩን ሂደት ለማሳለጥ የጐላ ሚና ያላቸው ሰራተኞች ስልጠናዎችን በማዘጋጀትና ስልጠና በመስጠት፣ በተለያዩ የምርምር እና ልማት መድረኮች ሳይንሳዊ እና ምርምሩን ለማሳለጥ የሚረዱ መመሪያዎችን፣ ደንቦችንና ሰነዶችን በተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች በሚሰጥ አቅጣጫ ለሚያዘጋጁ ባለሙያዎች ከዚህ በታች በቀረበው መሰረት የማትጊያ ክፍያ ይፈፀማል፡፡

1. በአውደ ጥናት ላይ የጥናት ውጤቶችን ለሚያቀርቡ የውስጥም ሆነ የውጭ ባለሙያዎች በአንድ በቀረበ ጽሁፍ ብር 6,000 (ስድስት ሺህ ብር)፤
2. ለፕሮጀክቱ ውጤማነት ሲባል ክህሎትን መሰረት በማድረግ ስልጠና እንዲሰጡ ተጋብዘው ስልጠናውን ለሰጡ የተቋሙም ሆነ የአጋር ድርጅቶች ባለሙያዎች ከአንድ ቀን እስከ ሦስት ቀን ለሚሰጥ ስልጠና ብር 5,000 (አምስት ሺህ)፤ ከአራት ቀን እስከ ሰባት ቀን ለሚሰጥ ስልጠና ብር 7,000 (ሰባት ሺህ) እና ከሰባት ቀን በላይ ለሚሰጥ ስልጠና 10,000 (አስር ሺህ) ብር፤
3. በእቅድ በፕሮጀክቶች ለተያዙ አውደ ጥናት፣ ሴሚናር እና ስልጠና የመሳሰሉ ኩነቶችን እንዲያስተባብሩ በሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ለሚመደቡና የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአጥጋቢ ሁኔታ ለተወጡ አስተባባሪዎች ለእያንዳንዳቸው ብር 4,000 (አራት ሺህ ብር) ይከፈላል፡፡ የአስተባባሪዎቹ ብዛት እንደ ፕሮጀክቱ ውስብስብነት የሚለያይ ሆኖ ከ 1 እስከ 5 ሊደርሱ ይችላሉ፡፡
4. የተለያዩ የሶፍትዌር መተግበሪያዎች (ዳታቤዝ፣ ድረገፅ እና ሌሎች መተግበሪያዎች) ለሚያበለፅጉ ባለሙያዎች ክፍያዎች እንደ ፕሮጀክቱ ፈንድ ታይቶ በተቋሙ የበላይ ሀላፊ የሚወሰን ይሆናል፡፡
5. በእቅድ በፕሮጀክቶች ለተያዙ የተለያዩ ሳይንሳዊ ፅሁፎችን፣ ሪፖርቶችንና ማኑዋሎችን ለሚያዘጋጁ ባለሙያዎች ለእያንዳንዳቸው ብር 10,000 (አስር ሺህ) ብር ይከፈላል፡፡

መለስ ማርዮ ሰለሞ (ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

## አንቀጽ 18

## የውሎ አበልና አል ጋ ክፍያዎች

በውጭ ፈንድ የሚደገፉ ፕሮጀክቶች የታለመላቸውን ግብ ለመምታት በሚያስችል መልኩ መተግበር እንዲቻል በፕሮጀክቶች ትግበራ የሚሳተፉ ተመራማሪዎች፤ የአስተዳደር ሰራተኞችና ሌሎች ከፕሮጀክት ትግበራ ጋር ቀጥተኛ ተሳትፎ ያላቸው የተቋሙም ሆነ ከተቋሙ ውጪ የሚመጡ ባለሙያዎች በመስክ ጉዞ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ የሚከፈላቸው የቀን ውሎ አበል በፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ በፀደቀው የውሎ አበል ተመን መሰረት ይሆናል። ይሁን እንጅ በፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ በግልፅ ካልተቀመጠ የውሎ አበል ክፍያው በወቅቱ ባለው ምንዛሬ ዋጋ መሰረት ተሰልቶ በብር እንደሚከተለው ይፈፀማል፡፡

ሠንጠረዥ 1፤ በውጪ ፈንድ የሚደገፉ ፕሮጄክቶች የውሎ አበል ተመን

| ተ.ቁ | የስራ መደቡ መጠሪያ | የውሎ አበል (በአሜሪካን ዶላር) |
|---|---|---|
| 1 | ጀማሪ ተመራማሪ | 25 |
| 2 | ረዳት ተመራማሪ I | 25 |
| 3 | ረዳት ተመራማሪ II | 25 |
| 4 | ተባባሪ ተመራማሪ | 25 |
| 5 | ተመራማሪ I | 25 |
| 6 | ተመራማሪ II | 25 |
| 7 | ከፍተኛ ተመራማሪ | 30 |
| 8 | መሪ ተመራማሪ | 30 |
| 9 | ለመሪ ሥራ አስፈጻሚ፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ሥራ አስፈጻሚ | 30 |
| 10 | ለዋና ዳይሬክተር፣ ለምክትል ዋና ዳይሬክተር | 35 |
| 11 | ለቴክኒክና ለአስተዳደር ባለሙያዎች | 20 |

መለሰ ማርዮ ሰላሞ(ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

# ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 19

### ተፈጻሚ ስለማይሆኑ ህጎች እና አሰራሮች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያና አሰራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት የለውም፡፡

### አንቀጽ 20

### መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ጥቅምት 22 ቀን 2016 ዓ.ም

መለሰ ማሪዮ (ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር

አዲስ አበባ